DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS
Office of Teaching and Learning

# የመኖሪያ ቤት እና የሆስፒታል የትምህርት-አሰጣጥ ፕሮግራም (Home and Hospital Instruction Program (HHIP) - የወላጅ የመመሪያ-መጽሐፍ

## ማውጫዎች


አጠቃላይ ምልከታ: 'HHIP' ምንድነው? ..... 3

ይህ መመሪያ፣ ማንን-ለመርዳት የተቀረጸ-ነው? ..... 4

የመመራት ሂደት (Referral Process) & የሕክምና ሰርቲፊኬት-የማቅረብ (Medical Certification) መስፈርቶች..... 4

የተሰጡ አገልግሎቶች ..... 4

የቀለም-ትምህርት/Academic የትምህርት-አሰጣጥ..... 5

ተዛማጅ የሆኑ አገልግሎቶች (Related Services) ..... 6

ወደ ትምህርት ቤት ተመልሶ-ለመመለስ፣ ሽግግርን ማቀድ ..... 6

እርጉዝ ተማሪዎች..... 6

የወሊድ ፈቃድ/Maternity Leave ..... 7

የአዕምሮ ህክምና እንክብካቤ (Psychiatric Care)ን የሚያገኙ ተማሪዎች ..... 7

ከ'አይኢፒዎች (IEPs)' ጋር የሚገኙ ተማሪዎች ..... 7

ለ'HHIP' አገልግሎቶች - የጊዜ-ሰሌዳን ማውጣት ..... 8

ከፕሮግራሙ የሚጠበቁ-ነገሮች..... 8

በትምህርት-ገበታ መገኘት/Attendance..... 8

ቦታ ..... 8

የመማሪያ አካባቢ/Learning Environment ..... 8

ለተማሪዎች፤ የአዋቂዎች ቁጥጥር መኖር ..... 9

ለተማሪ የቀለም-ትምህርት/ተዛማጅ የሆኑ አገልግሎቶች (Related Services) - የቤተሰብ እርዳታ..... 9

መሰረዝ እና ሳይደረጉ-የቀሩ ክፍለ-ጊዜዎች (Cancellations and Missed Sessions) 9

የደህንነት-ጥበቃ ቅድመ-ሁኔታዎች (Safety Precautions)..... 10

የቤት-ስራዎች (Assignments)፣ የደረጃ-አሰጣጦች (Grades)፣ እና የክንውን-እድገት ሪፖርቶች ..... 10

ጥያቄዎች እና ስጋቶች - አሏችሁ..... 11

ይግባኝ-ማለት/አቤቱታ ማቅረብ (Appeals) ..... 11

የDCPS የ'HHIP' ቢሮ..... 11

የዲሲ የስቴት የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (DC Office of State Superintendent of Education (OSSE)11

አባሪ (Appendix) A ..... 12

## አጠቃላይ ምልከታ: 'HHIP' ምንድነው?

የዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS)፣ የመኖሪያ ቤት እና የሆስፒታል የትምህርት-አሰጣጥ ፕሮግራም (Home and Hospital Instruction Program (HHIP)፤ በሕክምና በተረጋገጠ በሽታ - በአካላዊ ወይም አዕምሮአዊ ሁኔታ፣ በባህሪው አጣዳፊ ወይም ከባድ-ሁኔታዎችን በመፍጠሩ በመኖሪያ ቤት ወይም በሆስፒታል ውስጥ ለሁለት (2) ሣምንታት ወይም ከዚያ-በላይ - ከጊዜ-ወደ ጊዜ ተገድበው-እንዲቆዩ የሚያደርጋቸው፣ በመደበኛ የትምህርት ዓመቱ ውስጥ መመራት/referral የገባላቸውን ተማሪዎች - ጊዜያዊ የትምህርት-አሰጣጥን በመስጠት እርዳታ ያደርጋል።

ተማሪው በሕክምና ተገድቦ-የተቀመጠ ነው ተብሎ ከግምት-ውስጥ ሊያስገባው የሚችለው - የሚከተሉትን በሚኖሩበት ሁኔታ ነው:

- ሕክምና አስፈላጊ-በሚሆን ጊዜ፤
- መኖሪያ ቤቱን ለቅቆ መሄድ በሚያቅትበት-ጊዜ። ማንኛውም ከመኖሪያ ቤት መቅረቶች/absences በተደጋጋሚ የሆኑ፣ በአንፃራዊነት ለአጭር ጊዜ የሚቆዩ፣ ወይም የጤና እንክብካቤ ሕክምናን ለማግኘት የተደረጉ-ናቸው፤ <u>እና</u>
- አጣዳፊ የሆነ ሕክምና ከዕለታዊ በትምህርት-ቤት መገኘት ጋር መስተጓጉልን የሚፈጥር (ለምሳሌ፤ በሕክምና-ተቋም ውስጥ ሆኖ መታከም፣ የሕክምና ቀጠሮዎች በትምህርት ቤት ቀኑ ሰዓታት ዙሪያ - ከአራት እስከ አምስት ቀናት በሣምንት የሚፈልግ-ከሆነ)።

የDCPS 'HHIP' ቀደምታዊ ግቡ የሆነው፤ የተማሪውን ትምህርታዊ አካባቢ አገልግሎትን ከማግኘት እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮችን ማስወገድ-ነው። በተቻለ-መጠን ሁሉ፤ በትምህርት ቤት ማህበረሰባቸው አባላቶች ሆነው መቆየታቸውን ለማረጋገጥ መቻል፣ የልጆቹ ተመራጭ-የሆነ ፍላጎት ነው። የ'HHIP' ቢሮ የማዕከላዊ አገልግሎቶች፣ በትምህርት ቤት ውስጥ- መሠረት ባደረገው በ'HHIP' ቡድን፤ ተማሪውን ወደ በይበልጥ ጥበቃ-ባለው የመማሪያ አካባቢ ውስጥ ከማስገባቱ በፊት፣ የተማሪው ትምህርታዊ ፍላጎቶች መደገፉን ለማረጋገጥ ይሠራል። የተማሪው፣ የሕክምና ፍላጎቶቹ - በትምህርት ቤት በትምህርት-ገበታ መገኘት ላይ ተጽዕኖ ያለው በሚሆን-ጊዜ፣ ተገቢ-የሆኑ ማመቻቻዎችን በማቅረብ የ'HHIP' ቡድኑ መፍትሄ ለመፍጠር ሙከራ-ያደርጋል።

የ'HHIP' አገልግሎቶች፣ ትምህርታቸውን በመኖሪያ ቤት እንዲያገኙ፣ በተማሪው ወይም በቤተሰብ ምርጫ-ላይ መሠረት አድርጎ የሚሰራ አይደለም። DCPS፣ በመኖሪያ-ቤት ማስተማሪያ ፕሮግራም (homeschooling program) የለውም። 'HHIP' መሠረት-ያደረገው፣ በሕክምና ምክንያት በውሱንነት-እንዲገደብ በሚያስፈልገው ሁኔታ ላይ፣ ጉልህ የሆነ የሕክምና እክልን ለመከላከል ነው። DCPS፣ ሕክምናውን ከሚሰጠው ሐኪም ጋር - በትምህርት ቤት ህንፃ ውስጥ የትምህርት-አሰጣጥን ለማግኘት ተማሪው የማይችል መሆኑን - ሕክምና የሚያስፈልገውን የሚያሳይ፣ በአሁኑ-ጊዜ ስለአለው የሕክምና የመረጃ-ስብስብ (data)፣ መረጃን-ለመሰብሰብ አብሮ ይሠራል። የ'HHIP' መመራት/referralን ማስገባት፣ ወዲያውኑ ወደ 'HHIP' አገልግሎቶች ተማሪው እንዲገባ ፈቃድ-ለመስጠት ዋስትና-አለው ማለት-እንዳልሆነ ማስታወስ በጣም-አስፈላጊ ነው። DCPS፣ ወደ ትምህርት ቤት ተገኝቶ በትምህርት-ገበታ መገኘት እንቅፋቱ ሊወገድ-የሚችል መሆኑን-የሚወስን ይሆናል።

ወደ ትምህርት ቤት መጥቶ-በትምህርት ገበታ በመገኘት ላይ ያሉት እንቅፋቶች መወገድ በማይችልበት ጊዜ እና ተማሪው ወደ 'HHIP' አገልግሎቶች ብቁነትን ያገኘ ሆኖ ከተገኘ፤ የ'HHIP' ቡድኑ፣ ተማሪዎችን በመማሪያ-ክፍሎቻቸው እና ከመማሪያ-ክፍል አስተማሪዎቻቸው ጋር - እስከተቻለው የጊዜ-ድረስ - ወደ ሚማሩበት ትምህርት ቤታቸው ስኬታማ የሆነ ሽግግር እንዲኖራቸው ካላቸው ግብ-ጋር ሆነው፣ በርካታ ዘዴዎችን በመጠቀም -ይሰራሉ።

**ማስታወሻ፡ ‘HHIP’፣ የመኖሪያ-ቤት ማስተማሪያ (Homeschooling) አይደለም**

ሁለቱም ‘HHIP’ እና በመኖሪያ-ቤት ትምህርት (homeschooling) - የትምህርት-አሰጣጥን ከመኖሪያ-ቤት ተማሪዎች ከማግኘት ጋር የተያያዘ አገልግሎት የሚሰጡ ሆነው ቢገኙም፤ በጣም በተለያየ ዓላማዎች ላይ ሆነው አገልግሎት እንደሚሰጡ ማስታወስ-በጣም አስፈላጊ ነው። DCPS፤ የ‘HHIP’ አገልግልቶችን - በሕክምና ምክንያት ተወስነው እንዲቆዩ ለተደረጉ - በዚህ ሰነድ ውስጥ በተገለጸው መሠረት፣ ለDCPS ተማሪዎች አገልግሎት የሚሰጥ-ነው። ተማሪዎቻቸውን በመኖሪያ-ቤት ማስተማር (homeschool) ለማስተማር የሚፈልጉ ወላጆች እና አሳዳጊዎች፤ ተማሪው በመኖሪያ-ቤት ለመቆየት በሕክምና-የሚያስፈልገው መሆኑን ማሳየት አያስፈልጋቸውም፤ በስቴት የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (Office of State Superintendent of Education (OSSE) የሚፈለግባቸውን - በመኖሪያ-ቤት የማስተማር (home schooling) መስፈርቶችን ማሟላት እና ለ‘OSSE’፣ በመኖሪያ-ቤት ማስተማር (homeschool) የማድረግ ያላቸውን ዓላማ ማሳወቅ ያስፈልጋቸዋል። ተማሪዎቻቸውን በመኖሪያ-ቤት ለማስተማር

## ይህ መመሪያ፣ ማንን-ለመርዳት የተቀረጸ-ነው?

ይህ መመሪያ፤ ለDCPS ተማሪዎች - ወላጆች እና አሳዳጊዎች - ቢያንስ ከሚከተሉትን አንድ (1) ሁኔታዎች ላላቸው ነው:

- ወደ 'HHIP' ቢሮ መመራቱ/referral ከገባበት-ጊዜ ጀምሮ፣ በመኖሪያ-ቤት ወይም በሆስፒታል ለሁለት (2) ሣምንታት ወይም ከዚያ በላይ - በሕክምና ምክንያት ተወስኖ-መቆየት (ከላይ በተገለጸው መሠረት) ወይም ሊደርስ-ይችላል ተብሎ የሚገመት ተወስኖ-መቆየት፤ ወይም
- የወሊድ ፈቃድ/Maternity Leave፣ የሚያስፈልግበት ሁኔታ።

## የመመራት ሂደት (Referral Process) & የሕክምና ሰርተፊኬት-የማቅረብ (Medical Certification) መስፈርቶች

የ'HHIP' የመመራት ሂደት (referral process)፣ ወላጅ/አሳዳጊ - በሕክምና ተወስኖ-በመቆየት ወይም ሊደርስ-ይችላል ተብሎ በሚገመት ተወስኖ-በመቆየት ወይም በወሊድ ፈቃድ/maternity leave ምክንያት - የ'HHIP አገልግሎቶችን ለልጃቸው ለመጠየቅ - የትምህርት ቤታቸውን ርዕሰ-መምህር ወይም የ'HHIP ተወካይን በሚያነጋግሩ-ጊዜ፣ የሚጀምር-ይሆናል። የ'HHIP' አገልግሎቶችን ለማግኘት ጥያቄውን በተቀበለ በሁለት (2) የትምህርት ቀናቶች ውስጥ፣ የትምህርት ቤት ርዕሰ-መምህር ወይም የ'HHIP ተወካይ - አስፈላጊ የሆኑትን ቅጾች እንዲገኙ-የሚያደርጉ እና ለ'HHIP' ጥያቄን-ለማስገባት የሂደቱን መረጃዎች ያቀርባል።

ወደ 'HHIP' መመራቱ/referral፤ አምስት (5) ቅጾችን ሞልቶ-ማጠናቀቅ የሚያስፈልግ-ሲሆን፤ ይኸውም ለልጃችሁ ትምህርት ቤት የ'HHIP' ተወካዩ፣ የሚያጋራችሁ-ይሆናል። እነርሱን-ለማጠናቀቅ ኃላፊነት ያላቸው ቅጾች እና አካል/party - የሚከተሉትን ናቸው:

| የቅጽ ስም | ተሞልቶ-የተጠናቀቀው፣ በሚከተለው-ነው |
|---|---|
| ትምህርት ቤት አገልግሎት-እንዲሰጥ ይጠይቃል | የትምህርት ቤት፣ የ'HHIP' ተወካይ |
| የክትባት/Immunization ማረጋገጫ | የትምህርት ቤት ነርስ |
| የሐኪም ማረጋገጫ | የሚገድብ-ምርመራውን/confining diagnosis የሚያክመው፣ የተማሪው ሐኪም |
| የወላጅ/አሳዳጊ ስምምነት | ወላጅ/አሳዳጊ |
| ለማጋራት/Share ለማድረግ፣ ስምምነት መስጠት | |

ተማሪውን በመኖሪያ-ቤት ውስጥ ወይም በሆስፒታል ውስጥ ተወስኖ-እንዲቆይ ያደረገውን የሕክምና-ሁኔታው ላይ ህክምና የሚያደርገው ሐኪም፣ የ'HHIP' የሐኪም ማረጋገጫ ቅጽ (HHIP Physician Verification form)ን ሞልቶ ማጠናቀቅ-አለበት። ለምሳሌ፤ የተማሪው የሕክምና-ውጤት ነቀርሳ/ካንሰር ከሆነ፣ በዋና-ተቀዳሚ የሕክምና ሰጪው ሳይሆን በተማሪው ኦንኮሎጂስት - የ'HHIP' የሐኪም ማረጋገጫ ቅጹ (HHIP Physician Verification form)፣ ተሞልቶ-መጠናቀቅ አለበት። አንድ-ጊዜ ይህ ቅጽ ተሞልቶ-ከተጠናቀቀ እና ከገባ በኋላ፣ የ'HHIP' ቢሮው -አካሚውን-ሐኪም አግኝቶ ያነጋግራል። ለአገልግሎቶች የብቁነት አወሳሰኑ፣ በአምስት (5) የቀን-መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ - አንድ-ጊዜ ሁሉም ቅጾች ከገቡ-በኋላ የሚከናወን፣ እና ወላጅ/አሳዳጊ ስለ ውሳኔ-አሰጣጡ እንዲያውቁት-ይደረጋል። ሆኖም ግን፣ ሐኪሙን ለማነጋገር የሚኖር ማንኛውም መዘግየት፣ ለአገልግሎቶቹ የብቁነት አወሳሰን ላይ መዘግየትን-ሊያስከትል ይችላል።

የ'HHIP' አገልግሎቶቹ ከመጀመሪያው 60 ቀናት ባለፈ-ሁኔታ የሚያስፈልግ-ከሆነ፣ አዲስ የ'HHIP' የሐኪም ማረጋገጫ ቅጹ (HHIP Physician Verification form) - የመጀመሪያውን ቅጽ ሞልቶ-አጠናቅቆ ባስገባው ሕክምናውን የሚያደርገው ሐኪም፣ መግባት-አለበት። ተማሪውን የሚያክመው ሐኪም ከተለወጠ፣ አዲስ ከሚያክመው ሐኪም የቀረበው የ'HHIP' የሐኪም ማረጋገጫ ቅጽ (HHIP Physician Verification form) - ለ'HHIP' አገልግሎቶች እንደ አዲስ-መመራት/referral ሆኖ ሂደቱ-ይካሄዳል። በተጨማሪም፤ ለ'HHIP' አገልግሎቶች አዲስ-መመራት/referral እና የ'HHIP' አገልግሎቶቹ እንዲቀጥ-ለማድረግ በየ-ትምህርት ዓመቱ - ሁሉም የ'HHIP' ቅጾች መግባት-አለባቸው።

የ‘HHIP’ አገልግሎቶችን ተማሪው በሚያገኝ-ጊዜ፣ በትምህርት ቤት መዝገባቸው ላይ - ተማሪው ተመዝግቦ የሚቆይ-ይሆናል። ይህ ሁሉንም-ተማሪዎች የሚመለከት ሲሆን፣ ከዲሲ ውጪ ሕክምናን የሚያገኙ ተማሪዎችን ጨምሮ - የሚመለከት-ነው።

## የተሰጡ አገልግሎቶች

የ‘HHIP’ አገልግሎቶች፣ በየግል-ሁኔታ የሚሰራ ሲሆን፣ ተማሪው የሚያስፈልጉትን ነገሮች ለማሟላት የሚሰጥ-ነው። የ‘HHIP’ አገልግሎቶችን - ተማሪው እንዲያገኝ ፈቃድ-በሚያገኝበት ጊዜ፣ ምን አገልግሎቶችን ተማሪው እንደሚያገኝ እና ጥቅም-ላይ የሚውሉትን ዘዴዎች የሚዘረዝር ዕቅድን - DCPS ያዘጋጃል።

'HHIP'፣ የማስጠናት አገልግሎት (tutoring service) - ወይም የርቀት (virtual) ትምህርት ቤት አይደለም፤ ስለሆነም አገልግሎቱ የአንድ-ለአንድ የትምህርት-አሰጣጥን *ላያካትት-ይችላል*።

<u>የቀለም-ትምህርት/Academic የትምህርት-አሰጣጥ</u>

'HHIP'፣ በተቻለ-መጠን፣ ተማሪዎች የመማሪያ ክፍላቸውን እና/ወይም የመማሪያ-ክፍል አስተማሪውን ለማግኘት የሚችሉበትን ሁኔታ ለማቅረብ ዓላማ-ያደርጋል። DCPS፣ ተማሪው ወደ ትምህርት ቤት በአካል-መጥቶ ለመማር የሚያግዱትን እንቅፋቶች ለማስወገድ ይሠራል። DCPS፣ የትምህርት አሰጣጡን ለማግኘት እንዲችሉ የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀማል፣ እና ተማሪው ለክፍሎቻቸው ተመራጭ-ሆኖ መሠረት የሚሆናቸውን ዘዴ ለመወሰን፣ ከ'HHIP' ቡድን ጋር - DCPS ይሠራል። የ'HHIP' አገልግሎቶች፣ ከትምህርት ቤት ሰዓታት በኋላ፣ ቅዳሜና-እሁዶች (weekends)ን ጨምሮ - ሊሰጥ-የሚችል ነው።

ሁሉም ተማሪዎች የትምህርት-አሰጣጥን ከDCPS አስተማሪ ማግኘት ያለባቸው እና የቤት ስራዎችን እና ግምገማዎችን ማጠናቀቅ-አለባቸው። የበለጠ ጥልቅ/profound እና ጠንከር ካለ ጉዳተኝነት ጋር ለሚገኙ ተማሪዎች - የትምህርት ዓይነት ዙሪያን ጨምሮ፤ ሁሉም ክፍሎች - የDCPSን ደረጃ/scope እና ቅደም-ተከተልን - ይከተላሉ። የ'HHIP' አገልግሎቶችን የሚያገኙ ተማሪዎች፣ ልክ በትምህርት ቤት እንደአሉት እኩዮቻቸው የሚያስፈልጋቸውን ስራ ማጠናቀቅ ያስፈልጋቸዋል፣ ይህም አንድ-ዓይነት ቁጥር እና ጥንካሬ-ያለውን የቤት/የክፍል ስራዎችን አካትቶ-መስራት አለባቸው። በተጨማሪም፤ የ'HHIP' አገልግሎቶች - ስራውን-ለማጠናቀቅ የሚያስፈልገውን ጊዜ - ካለምንም-ሌላ ሁኔታ (automatically) የሚጨምር-አይደለም።

ሆኖም-ግን፣ በሕክምና ምክንያት በመቅረት - በትምህርት ቤት ውስጥ ተጽዕኖ ሊያመጣ የሚችል በመደበኛነት ሊጠበቅ የሚችል ወደኋላ መቅረት ሊኖር-ስለሚችል፤ ከዚህ-ጋር በተያያዘ ያጡትን ትምህርት ለማካካስ እንዲቻል - ተማሪዎችን መርዳት ግባችን ነው። በተማሪዎች ተመራጭ-የሆነው ፍላጎታቸው የምንመራ እና የሕክምና ጉዳዮች ምክንያት ተማሪዎች ሙሉ-ለሙሉ ከመካፈል የሚያግዳቸው ነገር ሊኖር እንደሚችል እንረዳለን። በሕክም-ምክንያት፣ ትምህርታዊ-አገልግሎቶችን ከማግኘት እንቅፋቶች በሚኖሩበት ሁኔታዎች ወቅት፤ የ'HHIP' ቢሮ - ከትምህርት-ቤት ውስጥ መሠረት ያደረገ የ'HHIP' ቡድን ጋር፣ ስለተገቢ-የሆነ ትምህርታዊ ዕቅድ ለመነጋገር፣ ይገናኛሉ። በአንዳንድ ሁኔታዎች ውስጥ ሲታይ፣ በትምህርት-አሰጣጥ ውስጥ መሳተፍ አለመቻል፣ በምርቃት ላይ ተጽዕኖ ሊያመጣ ይችላል።

በትምህርት ቤት መሠረት ያደረገው የ'HHIP' ቡድን፣ ለተማሪው የእርዳታ ዕቅድን በሚቀርጽ-ጊዜ፣ የሕክምና ሁኔታውን/የምርመራ-ውጤቱ (diagnosis) እና ምልክቱ(ቶቹ)ን ከግምት-ውስጥ ያስገባል። ይህ የእርዳታ ዕቅድ - ማመቻቻዎች (accommodations)ን - እንደ አሳንሰር/elevator ማግኘት፣ ዕረፍት-ማግኘት፣ ቀስ-በቀስ የሚድረገው ሽግግር ከአንድ (1) ሣምንት እንዳይበልጥ፣ ወዘተ... ማድረግን ሊያካትት-ይችላል።

በተማሪው የሕክምና ሁኔታ ላይ መሠረት አድርጎ፣ ከኮርስ-ስራቸው ጋር ሆነው በጤናቸው ላይ እና በሕክምናው ውስብስብነት የሚመጡን ነገሮች ላይ ተማሪው ትኩረት አድርጎ እየቀጠለ-ባለበት ጊዜ፤ የቀለም-ትምህርት የኮርስ-ጫንን ለስኬት-እንዲመቻቸላቸው አድርጎ ለተማሪው በማቅረብ ላይ ውይይት-ማድረግ ላይ - DCPS ሃሳብ-ሊያቀርብ ይችል-ይሆናል።

ከዚህ ቀደም-በጠራቀሙት ፈቃድ-ያላገኙ መቅረቶች (unexcused absences)[1] ምክንያት፣ የወደቁባቸው ኮርሶች ያሏቸው ተማሪዎች፣ ወይም በተርሙ/term ውስጥ ሁሉንም ያመለጧቸውን የትምህርት-አሰጣጥ ለማግኘት በቂ-ጊዜ የሌላቸው፣ እና ሁሉንም ያመለጧቸውን ስራዎች ማጠናቀቅ ለማይችሉ (ለምሳሌ፤ ተርሙ ከማለቁ ሦስት ሣምንታት በፊት እና ተማሪው ምንም የኮርስ ስራ ያላጠናቀቀ ሲሆን)፣ የትምህርት-አሰጣጡ ሊሰጥ-የሚችል ሲሆን፣ ነገር-ግን የማለፊያ የደረጃ-ውጤት እና ክሬዲት አይሰጥም። በተጨማሪም፤ የክሬዲትን መልሶ ማነሳሻ (credit recovery) የሆኑ ኮርሶች/courses፤ ድጋፍ-የሚያገኙ አይደሉም።

ተማሪ፣ ከእንግዲህ በመኖሪያ-ቤት ወይም በሆስፒታል ውስጥ ተወስኖ-መቆየት ሳይኖርበት በሚቀር-ጊዜ፣ በትምህርት

ቤት በአካል-ተገኝቶ መማር-አለበት። በአንዳንድ-ሁኔታዎች፤ የተማሪው የሕክምና ሁኔታ፤ ተወስነው-እንዲቆዩ መደረጉ የማያስፈልግ ከሆነም-በኋላ ሊቀጥል-ይችል ይሆናል፤ እና በትምህርት-ቤት በአካል-ተገኝቶ መማር አለባቸው። ለአብነት-ያህል፤ የጭን-አጥንት ፍራክቸር (fractured femur) ያለው ተማሪ፣ በፍራክቸሩ/fracture ባህሪይ እና ቦታ ምክንያት - በመጀመሪያ በመኖሪያ-ቤት ውስጥ ተወስኖ-እንዲቆይ ሊያስፈልግ-ይችላል። ሆኖም-ግን፣ አንድ-ጊዜ ተማሪው ክብደት-መሸከም ሲችል ወይም ተገቢ-የሆነ የመንቀሳቀሻ ዲቫይስ ሲያገኝ፤ ምንም-እንኳን ስብራቱ እየዳነ-እያለ - ተማሪው በትምህርት ቤት ተገኝቶ ከማመቻቻዎች ጋር ለመማር-የሚችል ያደርገዋል። ከካንሰር ጋር የሚገኝ ተማሪ፣ በሆስፒታል ውስጥ የኪሞቴራፒ ሕክምናውን ተኝቶ-ታካሚ ሆኖ በሚያገኝበት ጊዜ፤ ተወስኖ-መቆየት/confined ለመሆን ይችላ-ይሆናል።

---

[1] በDCPS ውስጥ፣ የሁለተኛ-ደረጃ ተማሪዎች - ከ30 ቀናት በላይ ፈቃድ ያላገኘ መቅረቶች (unexcused absences)ን ካጠራቀሙ፣ ካለምንም-ሌላ ሁኔታ (automatically) በኮርሱ ይወድቃሉ። ተጨማሪ-መረጃዎችን ለማግኘት፣ *በትምህርት-ገበታ ላይ መገኘት እና የመቅረት ፖሊሲ* (*Attendance and Truancy Policy*) - ‘Section H’ን በhttps://dcps.dc.gov/node/1556811. ላይ ተመልከቱ።

ሆኖም-ግን፤ በሕክምና ዑደቶቹ መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ - ተማሪው የሕክምና ቀጠሮዎች በሌሉት ጊዜ፤ በመኖሪያ-ቤት ወይም በሆስፒታል ተወስኖ-መቆየት ውስጥ ከእንግዲህ-የማይቀጥሉ፣ እና የሚቀጥለው የሕክምና ዑደት እስከሚደርስ ድረስ በትምህርት-ቤት ገብተው መማር-የሚችሉ ያደርጋቸዋል።

ተዛማጅ የሆኑ አገልግሎቶች (Related Services)
በየግል የትምህርት ፕሮግራም (Individualized Education Program (IEP) ወይም በ'Section 504' ዕቅድ ላይ ተዛማጅ የሆኑ አገልግሎቶች ( related services) የታዘዘላቸው ተማሪዎች፣ በሕክምና ተገቢ በሆነበት ጊዜ - ተዛማጅ የሆኑ አገልግሎቶች (related services)ን ለማግኘትም ብቁ-ናቸው። በተማሪው የሕክምና ፍላጎቶች ላይ መሠረት አድርጎ - በተመራጭ የሆነው የተማሪውን ፍላጎት ምን-እንደሆነ ለመወሰን፣ DCPS ከተማሪው የሕክምና አገልግሎት-ሰጪው ጋር አብሮ-የሚሰራ ይሆናል። በአንዳንድ-ሁኔታዎች ውስጥ፤ የ'HHIP' ቡድን የአገልግሎቶቹን መቀጠል ከግምት-ውስጥ ካስገባ በኋላ፤ ቡድኑ - የታዘዙት አገልግሎቶች በሙሉ ለተማሪው ተገቢ እንዳልሆኑ ሊወስ-የሚችል እና የተማሪው አይኢፒ (IEP) ወይም 504 ቡድን - የተማሪውን አይኢፒ (IEP) ወይም 504 ዕቅድ በጊዜያዊነት ለማስተካከል ሊወስን-ይችል ይሆናል።

በ'HHIP' ላይ እያሉ - ለተማሪው የተመደቡት የተዛማጅ የሆኑ አገልግሎቶች (Related service) አገልግሎት-ሰጪዎች፣ በትምህርት ቤት-መሠረት ካደረጉት አገልግሎት-ሰጪዎች ሊለዩ-ይችሉ ይሆናል።

ወደ ትምህርት ቤት ተመልሶ-ለመመለስ፣ ሽግግርን ማቀድ
በተወሰነ-ቦታ የመቆየት (confinement)[2] መስፈርትን-ማሟላት ከእንግዲህ-የማያስፈልጋቸው በሚሆን ጊዜ፤ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት ተመልሶ-መግባት ያስፈልጋቸዋል። ይህ በ'Physician Verification' ቅጹ ላይ የተፃፈው ቀን ከማለቁ በፊት ሊሆን-ይችላል፤ እና ዓላማው-በተቻለ መጠን፣ ተማሪው ወደ ትምህርት ቤት ሙሉ-ለሙሉ እንዲሸጋገር ማድረግ-ነው። ማመቻቻዎች፤ እንደ 'ADA accessibility' ያሉት፤ ተማሪው ወደ ትምህርት ቤት ተመልሶ ለመሸጋገር መቻሉን ለማረጋገጥ፣ በDCPS ከግምት-ውስጥ የሚገባ ነው።

## እርጉዝ ተማሪዎች

እርጉዝ-የሆኑ ወይም የሚሆኑ ተማሪዎች፣ ለመውለድ እስከሚገቡ ድረስ ወይም በእርግዝና ውስብስብ-ሁኔታዎች ምክንያት ሆስፒታል-ካልገቡ በስተቀረ፣ በትምህርት ቤት ተገኝተው መማራቸውን መቀጠል ያስፈልጋቸዋል። በእግዝና ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ያሏቸው ምልክቶች፤ እንደ ማቅለሽለሽ፣ ድካም፣ የአካል-አለመመቻቸት፣ ወይም እብጠት - በትምህርት ቤት ውስጥ እንደሚከሰቱ የሚጠበቅ ነው፤ ሆኖም ግን DCPS - በተቻለ-መጠን፣ ለእርጉዝ ተማሪዎች ማመቻቻዎችን በተገቢው-ሁኔታ ከግትም-ውስጥ ያስገባል። ለአብነት-ያህል፣ እርጉዝ ተማሪዎች - የሚከተሉትን ማመቻቻዎች ለማግኘት ብቁ-ሊሆኑ ይችሉ ይሆናል:

- አሳንሰር/elevator - መጠቀም፣
- በክፍሉ-ወቅት፣ መክሰሶች/snacks እና በጠርሙስ-የሚገኝ ውሃ (water bottle) - እንዲገኝ-ማድረግ፣
- ትራስ-መጠቀም፣
- እግርን-ከፍ ማድረግ፣
- የመንቀሳቀስ የዕረፍት-ጊዜያቶች፣
- በተለየ አካባቢ ምሣ መብላት፣
- በክፍሎች-መካከል ሽግግር-ለሚደረግበት ጊዜ ተጨማሪ-ጊዜን መስጠት
- ተመራጭ የሆነ የመቀመጫ ቦታ (Preferential seating)፣
- በነርስ ክፍል (nurse's suite) ውስጥ ዕረፍት-ማድረግ፣
- ተማሪ-ያልሆኑ የሚጠቀሙበትን የመጸዳጃ-ቤት መጠቀም፣ ወይም
- ዩኒፎርም ያልሆነ ልብስን ለመልበስ ፈቃድ-ማግኘት (ለምሳሌ፤ የተመቻቸ-ስሜት የሚሰጣቸውን ሱሪ)።

ከእርግዝና-ጋር በተገናኘ ምልክቶች ምክንያት፣ በክፍል-ውስጥ አንዳንድ ተማሪዎች ትኩረት-አድርገው ለመቆየት ያለው ችሎታቸው የመቀነስ ተሞክሮ ሊገጥማቸው-ይችላል። DCPS፤ እስከተቻለበት ደረጃ ድረስ - አለመቻቸትን ሊያጠፋ የሚችል

**HHIP Parent**

ማስተካከያን ለመፍጠት መስራት እና በተማሪው ላይ ተጽዕኖ ሊያመጡ የሚችሉ በርካታ እንቅፋቶች እንዳሉ አስተማሪዎች እና ሠራተኞች ግንዛቤ-እንዳላቸው ለማረጋገጥ - በትምህርት ቤት መሠረት-ከአደረገ የ‘HHIP’ ቡድን ጋር አብሮ-ሆኖ ይሠራል።

[2] ለ“confinement,” ትርጓሜው/definition - ለማግኘት *አጠቃላይ-ምልከታ (Overview): What is HHIP?* የሚለው ክፍል ከላይ ተመልከቱ።

<u>የወሊድ ፈቃድ/Maternity Leave</u>

የወሊድ ፈቃድ/Maternity leave፣ ከዚህ-ቀደም እርጉት ለነበሩ ተማሪዎች፣ ልጁ ከተወለደበት ቀን ጀምሮ ለስድስት (6) ሣምንት ይሰጣል። በቀዶ-ጥገና ወሊድ ( cesarean section) የተከናወነ-ከሆነ፣ እስከ ስምንት (8) ሣምንት ይራዘማል። በየግል-ሁኔታዎች ምክንያት - እንደ የልጅ-እንክብካቤ (childcare)ን ባለማግኘት ምክንያት፣ የወሊድ ፈቃድ/Maternity leave ሊራዘም-አይችልም። የ'The New Heights Coordinator' (የተመደበ-ካለ) እና በትምህርት ቤት ውስጥ መሠረት ያድረገ የ'HHIP' ቡድን፤ ተማሪው ወደ ትምህርት ቤት ለመመለስ እንቅፋት የሚሆኑ ተጽዕኖ በሚገጥመው-ጊዜ፣ የእርምጃ ዕቅድ/action planን ለተማሪዎ ለመቅረጽ - አብረው ይሠራሉ። ከወሊድ ፈቃዳቸው (maternity leave) እና የ'HHIP' አገልግሎቶች ሲጠናቀቁ፤ ሁሉም ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት መመለስ ይጠበቅባቸዋል።

በወሊድ ፈቃድ/Maternity leave ወቅት-ላይ፣ የተማሪው የቀለም-ትምህርት የጊዜ-ሰሌዳ ሊስተካከል-ይችላል። ትምህርት ቤት እና ወላጅነት የሚጠብቅባቸው-ነገሮች እንዴት በተማሪው የትምህርት-አሰጣጥን በመቀበል ላይ እና የቤት-ስራዎችን በሁሉም ኮርሶች በማጠናቀቅ ላይ ተጽዕኖ ሊያመጣ እንደሚችል - 'HHIP' ከግምት-ውስጥ ያስገባል። አንድ ወይም ከዚያ-በላይ ክፍሎች ለጊዜ-እንዲቋረጡ/paused በሚደረጉበት ሁኔታዎች ወቅት፣ ወደ ትምህርት ቤት ተማሪው በሚመለስበት ጊዜ፣ ሁሉንም ያልተሰሩ የቤት-ስራዎች (assignments) አካክሶ-መጨረስ ያስፈልጋቸዋል። የ'HHIP' ቢሮ፣ በትምህርት ቤት መሠረት-ካደረገ የ'HHIP' ቡድን ጋር አብሮ-በመስራት፣ ተማሪው በኮርሱ የመጨረሻ የደረጃ-ውጤትን እንዲያገኝ ዕድል-እንዲኖረው ለማድረግ የማካካሻ ዕቅድ (make-up plan) ለመቅረጽ አብረው-ይሠራሉ።

## የአዕምሮ ህክምና እንክብካቤ (Psychiatric Care)ን የሚያገኙ ተማሪዎች

በትምህርት ቀኑ ወቅት ላይ ጠንከር-ባለ የአዕምሮ ህክምና (psychiatric treatment) ፕሮግራሞች ውስጥ የሚሳተፉ ተማሪዎች፣ እንደ - ተኝቶ-ታካሚ የሆስፒታል ፕሮግራም ውስጥ ወይም በከፊል የሆስፒታል ውስጥ ፕሮግራም ባሉት-ውስጥ የሚሳተፉ፤ በሕክምናቸው ወቅት ትምህርታቸውን ለመማር የሚገኙ ላይሆኑ-ይችላሉ። የ'HHIP' ቡድን፣ መቼ ተገቢ-የሆነ ትምህርታዊ አገልግሎቶችን ማስጀመር እንደሚገባ - እንዲሁም ተማሪው በሕክምና-ላይ እያለ ማግኘት-የሚገባውን ተገቢ-የሆኑ የኮርሶች ቁጥርን - ለመወሰን፣ ከትምህርት ቤት የአዕምሮ-ህክምና ባለሙያ ቡድን (psychiatric team) ጋር አብሮ-ይሰራል። በአንዳንድ-ሁኔታዎች ውስጥ፣ በሆስፒታል-ውስጥ መግባት - የተማሪውን ወደ ሌላ-ክፍል የማለፍ ሁኔታውን ወይም የታቀደላቸውን የምርቃት ቀን ላይ ተጽዕኖ ሊያመጣባቸው ይችላል።

ጠንከር-ባለ እየተመላለሱ በሚታከሙ በሽተኞች ፕሮግራም (intensive outpatient program (IOP) ውስጥ የሚሳተፍ ተማሪዎች - በከሰዓት-በኋላ ውስጥ በሚጀምረው ውስጥ ያሉ፤ በቀኑ በትምህርት ቤት ተገኝተው-መማር አለባቸው። በተለመደ-ሁኔታ፤ ተማሪዎች በአብዛኛው የትምህርት ቀኑ ወቅት-ላይ፣ በተቻለ መጠን በትምህርት ቤት ተገኝተው መማራቸውን ለማረጋገጥ፣ ይህ 'IOP' የሚጀምረው ከተለመደው የትምህርት ቀን በኋላ ነው። በ'IOP' መጀመሪያ-ሰዓቱ ምክንያት ተጽዕኖ የሚደርስባቸውን የከሰዓት-በኋላ ኮርሶችን በመደገፍ ዕቅድ-በማውጣት ላይ፣ የ'HHIP' ቢሮ - በትምህርት ቤት መሠረት ካደረገው የ'HHIP' ቡድን ጋር አብሮ-ይሠራል።

በአዕምሮ-ሕመም እክል ላይ የሚገኙ ተማሪዎች፤ በሆስፒታል-ውስጥ በመግባታቸውን የተረጋገጠላቸው፤ ትምህርታቸውን ለማግኘት የማይችሉ ሊሆን ይችላል። በእነዚህ-ሁኔታዎች ወቅት፤ ተማሪው በቂ-በሆነ የሕክምና-አሰራር አገልግሎቶቹን ለማግኘት የተረጋጋ መሆኑ እስከሚወሰን ድረስ፣ ትምህርታዊ አገልግሎቶች ለጊዜው-እንዲቆሙ የሚደረግ-ይሆናል። ተማሪው ትምህርቱን ለማግኘት እንደሚችል በሚወሰን ጊዜ፤ የእገዛ ማድረጊያ ዕቅድ ይቀረፃል።

በሆስፒታል ውስጥ ገብተው የሚታከሙ (inpatient) ወይም በከፊል በሆስፒታል ፕሮግራም ውስጥ በተደጋገመ ሁኔታ የማይሳተፉ ተማሪዎች፤ ወደ ትምህርት ቤት መሸጋገር አለባቸው። ከስድስት (6) ሣምንታት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የሽግግር ዕቅድ (transition plan)ን ለማዘጋጀት፣ የ'HHIP' ቢሮው - በትምህርት ቤት መሠረት ካደረገው የ'HHIP' ቡድን ጋር አብሮ-ይሠራል። በስድስት (6) ሣምንታት ውስጥ ወደ ሙሉ-ለሙሉ የትምህርት ቀን ለመሸጋገር ተማሪው ካልቻለ፤ የሽግግር ዕቅዱ (transition plan) በጊዜያዊነት እንዲቆም-የሚደረግ እና ዳግም-ግምገማ ይደረግለታል። በአሁኑ-ጊዜ ባለው ሐኪም የሕክምና ዕቅድ ስር ካልተሟላ ወይም በአሁኑ-ጊዜ ያለው የሐኪም የህክምና ዕቅድ አጥጋቢ ሆኖ ካልተገኘ፤ ስለ ተዛማጅ-የሆነ የመረጃ-ስብስብ (relevant data)፣ ምልከታዎች፣ እና ስለ ማንኛውም ስር-የሰደደ የሕክምና ስጋቶች - ለመወያየት፣

DCPS ከሕክምና ቡድኑ እና ከቤተሰብ ጋር ለመነጋገር ጥያቄ-ያቀርባል። በሕክምና-ላይ መሠረት ያደረገ እርዳታን ለመስጠት (ለምሳሌ፣ ቴራፒ)ን ለተማሪዎች ለመስጠት፣ በDCPS ሰራተኞች ስልጣን-ስር እንዳልሆነ፣ እባካችሁ አስታውሱ። በDCPS ሠራተኞች የሚሰጠው እርዳታ፣ ተማሪው ትምህርትን ለማግኘት ባለው አቅም-ላይ ትኩረት የሚያደርግ ነው።

## ከ‘አይኢፒዎች (IEPs)’ ጋር የሚገኙ ተማሪዎች

ተማሪው ‘አይኢፒ/IEP’ ያለው ሲሆን እና የ‘HHIP’ አገልግሎቶች በሚያስፈልገው-ጊዜ፤ ተማሪው በታመመ-ጊዜ በሚያስፈልጉት-ነገሮች እና ባለው አቅም-ምክንያት፣ በ‘አይኢፒ/IEP’ው ላይ ማስተካከያ-መደረግ ሊያስፈልግ ይችላል።

ተማሪው የ'HHIP' አገልግሎቶችን እያገኘ-ባለበት ጊዜ - 'አይኢፒ/IEP'ው ላይ ማስተካከያ-ተደርጎ ከነበረ፤ ተማሪው ወደ ትምህርት ቤት መመለስ-ተከትሎ፣ የ'አይኢፒ/IEP' ቡድኑ ተሰብስቦ - 'አይኢፒ/IEP'ውን እንደገና ያስተካክላሉ።

## ለ'HHIP' አገልግሎቶች - የጊዜ-ሰሌዳን ማውጣት

ብዙዎቹ የሐኪም ቀጠሮዎች እና የሕክምና እርዳታዎች የሚሰጡት፤ በትምህርት ቀኑ ውስጥ ባለው ሰዓታት ውስጥ ነው። በሕክምና ቀጠሮዎች እና በትምህርት-አሰጣጥ ክፍለጊዜዎች መካከል - በቀጠሮ የጊዜ-ሰሌዳ አያያዝ ምክንያት የሚፈጠሩ የሰዓት-መዘባቶችን ለማስወገድ ሲባል፤ አገልግሎቶችን ለተማሪዎች 'HHIP' በሚሰጥበት ጊዜ፣ እንደ ከተለመደው የትምህርት ሰዓታት በኋላ-ባለው ጊዜ፣ በቅዳሜና-እሁድ ወቅት፣ ወይም በትምህርት ቀኑ ውስጥ - እርዳታን የመስጠት በርካታ ዘዴዎችን ይጠቀማል። ለእነዚህ የትምህርት-አሰጣጥ ክፍለጊዜዎች ተማሪዎች መገኘት የሚችሉ መሆን የሚጠበቅባቸው፣ እና በሕክምና-ቀጥሮአቸው ባልሆነ ምክንያት በ'HHIP' አገልግሎት የጊዜ-ሰሌዳቸውን ላይ መስተጓጎልን ፈጥረው የማከተሉ ከሆነ፣ በ'HHIP' በሚሰጠው የትምህርት-አሰጣጥ አገልግሎቶች ላይ - ተማሪዎች ክፍተት/gap እንዲፈጠር ሊያደርጋቸው ይችላል።

የ'HHIP' ክፍለጊዜዎች - በፌደራል እና በዲሲ የበዓል-ቀናቶች ላይ፣ በአስተማሪ ስራ/ዕቅድ-አወጣጥ ቀናቶች፣ በሙያ-ማሳደጊያ ቀናቶች፣ እና በወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንስ ቀናቶች ላይ፤ አይካሄዱም። 'HHIP' በተጨማሪም፣ በመጥፎ የአየር-ጠባይ ምክንያት ከDCPS መዘጋቶች እና ዘግይቶ-መጀመሮች ጋር ተከትሎ የሚካሄድ-ነው። በትምህርት ቤት መዘጋቶች ወይም ዘግይቶ-በመከፈታቸው ምክንያት ያመለጓቸው ክፍለጊዜዎች፣ ከተቻለ - ሌላ የጊዜ-ሰሌዳ የሚወጣላቸው ይሆናል። የትምህርት ቤት ዘግይቶ መከፈት፣ መዘጋቶች፣ የዕረፍት-ጊዜዎች፣ የበዓል-ቀናቶች፤ የ'HHIP' አገልግሎቶች እንዲራዘም አያደርጉትም።

## ከፕሮግራሙ የሚጠበቁ-ነገሮች

<u>በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት (Attendance)</u>

የተማሪ መቅረቶች/absences፤ የተጠናቀቀው የ'HHIP' መመሪት/referral - በ'HHIP' ቢሮ ከተቀበሉበት ቀን ጀምሮ - ፈቃድ እንዲያገኙ (excused እንዲሆኑ) ይጠየቃል። ለ'HHIP' አገልግሎቶች ተማሪው አንድ-ጊዜ ብቁ-የማይሆን ሲሆን፣ በአካል-ተገኝቶ በትምህርት-ገበታ ከመማር ሊያገኙት የሚችሉበትን-ፈቃድ (excused ሊሆኑ) አይችሉም። የ'HHIP' አገልግሎቶች በሚቋረጡ ጊዜ፣ የትምህርት ቤት በትምህርት-ገበታ መገኘት ቢሮ (attendance office) እንዲያውቀው የሚደረግ እና ከዚያም ተማሪው ተመልሶ-ወደ ትምህርት ቤት መግባት ይጠበቅበታል።

የ'HHIP' አገልግሎቶችን ተማሪው በሚያገኝበት ጊዜ፣ ለሕክምና-ባልሆነ 'ፈቃድ-የተሰጠው/excused'ን ለሦስት (3) የትምህርት-አሰጣጥ ክፍለጊዜዎች ተማሪው ሳይገባ ያመለጠው ከሆነ፤ በትምህርት-ገበታ መገኘት ላይ ያለው እንቅፋት ምላሽ እስከሚያገኝ-ድረስ እና ተማሪው በ'HHIP' ውስጥ ለመሳተፍ ዝግጁ-እስከሚሆን ድረስ - አገልግሎቶቹ ለጊዜው-እንዲቆም የሚደረግ መሆኑን፣ በትምህርት ቤት-መሠረት ያደረገው ቡድን እና ወላጅ/አሳዳጊዎች እንዲያውቁት ይደረጋል። በ'HHIP' ውስጥ ተማሪው ሙሉ-ለሙሉ መሳተፍ እስከሚችል ድረስ፣ ለሕክምና-ባልሆነ ምክንያት ፈቃድ-ከተሰጠው/excused ከሦስተኛው ቀን በኋላ ያመለጠው ክፍለ-ጊዜ፣ ፈቃድ የማያገኝ-ይሆናል።

የተማሪው ቤተሰብን ማነጋገር ካልተቻለ እና ተማሪው በክፍለ-ጊዜዎቹ ውስጥ የማይሳተፍ-ከሆነ፤ አግኝቶ-ማነጋገር እስከሚቻል እና ለመሳተፍ እንቅፋት የሆኑት-ምክንያቶች ምላሽ እስከሚያገኙ ድረስ፣ አገልግሎቶቹ ለጊዜው-እንዲቆም የሚደረግ መሆኑን፣ በትምህርት ቤት-መሠረት ያደረገው ቡድን እንዲያውቀው-የሚደርግ እና ቀሪነታቸውም ፈቃድ-የማያየኝ-ይሆናል።

ተማሪው ከመኖሪያ-ቤታቸው ወይም ከሆስፒታል ውጪ የሚሰሩ-ከሆነ፤ የ'HHIP' አገልግሎቶቹ ወዲያውኑ

እንዲቆም-ይደረጋል። <u>በታ</u>

**HHIP Parent**

ክፍለጊዜዎቹ (Sessions)፤ በተማሪው መኖሪያ-ቤት ወይም በሆስፒታል ውስጥ ይካሄዳል። ወላጆች/አሳዳጊዎች - ክፍለጊዜዎች በሌላ ቦታ - እንደ የዘመድ-ቤት ውስጥ እንዲደረግ - ለ'HHIP' ቢሮ ለመጠይቅ-ይችላሉ። ይህን-መሰል የቦታ ለውጥ፤ በ'HHIP' ቢሮ መጽደቅ-ያለበት እና ዋስትና-ያገኘም አይደለም። አገልግሎቶች፤ ከዋሽንግተን ዲሲ ውጪ ሊካሄዱ አይችሉም። ክፍለጊዜዎቹ-በተጨማሪም፤ የትምህርት-አሰጣጡን ማግኘት እንዲቻል-ለማድረግ በኮምፒውተር አማካኝነት ወደክፍሉ መግባት (logging into class) ያካተተም ሊሆን ይችላል።

<u>የመማሪያ አካባቢ/Learning Environment</u>

ተማሪዎች እና ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ የ'HHIP' ክፍለጊዜዎች የሚሰጥበት ተገቢ-በሆነ ሁኔታ ለመማር - የሚከተለውን በማካተት በአካል-ተገኝቶ የተዘጋጀ-ቦታ መኖሩን ማረጋገጥ-አለባቸው።

- ክፍለጊዜ የሚካሄድበት ቦታ፣ ንጹን እና ጥሩ-ብርሃን ያለው ነው።

- ተማሪው እና ሠራተኛው በክፍለ-ጊዜ ላይ ትኩረት ማድረግ እንዲችሉ ለማድረግ፣ በአካባቢው ሊኖር የሚችሉ የሚረብሹ-ነገሮች አነስተኛ-መሆን አለበት። ይህም የሚያካትተው፤ ቴሌቪዥን፣ ሙዚቃ፣ ቪዲዮ ጌሞች፣ ድምጽን ከፍ-አድርጎ የሚሰማ የሌሎች ንግግር፣ ከወንድምና-እህት የሚመጡ መስተጓጉሎች፣ ወዘተ...
- ለትምህርት-አሰጣጥ ክፍለጊዜው የሚሆኑ ሁሉም የሚያስፈልጉ ቁሳቁስ/material፣ በተማሪው መገኘት መቻል-አለበት።
- ተማሪው እና በመኖሪያ-ቤቱ ውስጥ የሚገኙ ሁሉም አባላቶች፣ በተገቢው-ሁኔታ ልብሳቸውን መልበስ አለባቸው (ማለትም፤ ሙሉ-ለሙሉ መልበስ፣ ከላይም እና ከታችሁ ሁለቱንም-የለበሱ)።
- ክፍለጊዜ ከመጀመሩ በፊት፣ ሁሉም የቤት-እንሰሶች (pets) ከማንኛውም ቦታዎች - የ'HHIP' አገልግሎት ሰጪው ከሚኖርበት ቦታዎች - እንደ ዋናው-መግቢያ በር/መግቢያ እና ክፍለጊዜው ከሚካሄድበት ክፍል መወገድ-አለባቸው። ለአጠቃላይ ክፍለጊዜው ወቅት፣ የቤት-እንስሳዎች (pets) - በተጠበቀ-ቦታ ውስጥ ሆነው እስካልተጠበቁ-ድረስ፤ አገልግሎት ሰጪው ወደ ቤት አይገቡም።
- አገልግሎት-ሰጪው በተገኘበት ጊዜ ላይ፣ በመኖሪያ-ቤት ውስጥ፤ ማጨስ-የተከለከለ ነው።
- በክፍለጊዜው ወቅት-ላይ ተማሪው መድኅኒት መውሰድ ያለበት ሆኖ ካልቀረበ በስተቀረ፤ መድኅኒቶች፣ ለመዝናኛነት-የሚውል መድኅኒት/drug paraphernalia፣ እና አልኮል-መጠጥ፤ በማንኛውም 'HHIP' አገልግሎት-ሰጪ በሚገባበት ቦታ፣ መኖር-የለበትም።
- ከመኖሪያ-ቤት ወይም ከሆስፒታል - ወደየ-ክፍሎቻቸው -ለሚገቡ (logging into ለሚያደርጉ) ተማሪዎች፤ ወደ ክፍሉ ከመግባታቸው በፊት፣ ያሉበት ቦታ ከላይ-ከተጠቀሱት አስተጓጓይ ሁኔታዎች የጸዳ-መሆኑ ማረጋገጥ አለባቸው።

ተማሪው ወይም ለክፍለጊዜው የሚሆነው ቦታ - አገልግሎት-ሰጪው በሚመጣበት ጊዜ ላይ ለመጀመር-ዝግጁ ሆኖ ካልተገኘ፣ አገልግሎት-ሰጪው እስከሚሰናዳ ይጠብቃል። ሆኖም-ግን፣ ተጨማሪ ሰዓት - ለክፍለጊዜው ላይጨመር ይችል-ይሆናል።

ከላይ-የተጠቀሱት የሚጠበቁ-ነገሮች የማይሟሉ በሚሆንበት-ጊዜ፣ ከመኖሪያ-ቤት ወይም ከሆስፒታሉ ለመውጣትና ለመሄድ እና ክፍለጊዜውን ወዲያውኑ ለመሰረዝ - የDCPS እና የአገልግሎት-ሰጪዎች መብታቸው-የተጠበቀ ነው። የሚጠበቁባቸውን-ነገሮች በማሟላት ላይ ተደጋጋሚ-የሆኑ ችግሮች ካሉ፤ መፍትሄው ላይ ውይይት እስከሚደረግበት እና በስምምነት-ላይ እስከሚደረስበት ጊዜ-ድረስ - ክፍለጊዜ ለጊዜው-እንዲቋረጥ/paused ይደረጋል።

<u>ለተማሪዎች፤ የአዋቂዎች ቁጥጥር መኖር</u>

የ'HHIP' አገልግሎት-ሰጪዎች በመኖሪያ-ቤት ውስጥ በሚደርሱበት ጊዜ፣ ለተማሪው ኃላፊነት የሚወስድ አዋቂ-ሰው በመኖሪያ-ቤት ውስጥ - በአጠቃላይ ክፍለጊዜው ወቅት ላይ - ተማሪው 18 ዓመት ወይም ከዚያ-በላይ ቢሆንም እንኳን፣ መገኘት መቻል አለባቸው። በክፍለጊዜው ወቅት - አዋቂው-ሰው መኖሪያ ቤቱን ልቅቆ-ከሄደ፣ የ'HHIP' አገልግሎት-ሰጪው - ወዲያውኑ ክፍለጊዜውን ያቆማል። ይህ መስፈርት፤ በተማሪው የሆስፒታል ክፍል ውስጥ የሚደረግ የ'HHIP' ክፍለጊዜዎችን ወይም አገልግሎቶች ላይ በስራ-ላይ የሚውል አይደለም።

የ'HHIP' አገልግሎት-ሰጪው በመኖሪያ-ቤቱ ውስጥ ሲደርስ - አዋቂ-ሰው ከሌለ፤ አዋቂው-ሰው እስከሚመጣ ድረስ - የ'HHIP' አገልግሎት-ሰጪው ውጪ-ይጠብቃል እና የተማሪውን ወላጅ/አሳዳጊን ለማነጋገር ሙከራ-ያደርጋል። አዋቂው-ሰው የጊዜ-ሰሌዳ የተያዘለት ክፍለጊዜ ከማለቁ-በፊት ከመጣ፤ አገልግሎት-ሰጪው ክፍለጊዜውን ይጀምር እና በጊዜ-ሰሌዳ ማብቂያው ሰዓት ላይ ያቆማል። ሳይሰጡ-ያመለጠ ሰዓት፣ የሚካካስ አይሆንም። የጊዜ-ሰሌዳው ሰዓት ከማለቁ-በፊት አዋቂው-ሰው ካልመጣ፣ ክፍለጊዜ የሚሰረዝ እና ሌላ-ተለዋጭ የጊዜ ሰሌዳ ወይም ማካካሻ-ክፍለጊዜ አይሰጥም።

<u>ለተማሪ የቀለም-ትምህርት/ተዛማጅ የሆኑ አገልግሎቶች (Related Services) - የቤተሰብ እርዳታ</u>

ወላጆች፤ ተማሪዎቻቸው ሙሉ-ለሙሉ በክፍለ-ጊዜዎቹ ውስጥ - ከአገልግሎት-ሰጪዎች ጋር ሆነው እና የቤት ስራዎቻቸውን በተቻል መጠን በራሳቸው-በመስራትና በማጠናቀቅ እንዲሳተፉ ማበረታታት አለባቸው። የቤት ስራዎች (Homework assignments)፣ ከአገልግሎት-ሰጪው ጋር ከሚደረገው የሚቀጥለው ክፍለጊዜ በፊት፣ መጠናቀቅ አለባቸው።

## መሰረዝ እና ሳይደረጉ-የቀሩ ክፍለ-ጊዜዎች (Cancellations and Missed Sessions)

በተማሪው ወይም በወላጅ/አሳዳጊ የሚደረግ-ስረዛዎች (Cancellations) - ቢያንስ 24 ሰዓታት ቀደም-ብሎ፣ በተቻለ-መጠን መደረግ-አለበት።

የ'HHIP' አገልግሎት-ሰጪዎች በተጨማሪም፣ የ24-ሰዓት ማስታወቂያን - ከክፍለጊዜው መሰረዝ በፊት፣ በተቻለበት ጊዜ ሁሉ - ያቀርባሉ። አገልግሎት-ሰጪው ክፍለ-ጊዜውን በሚሰርዝበት-ጊዜ፤ ሳይሰጡ የቀረው ክፍለጊዜ - በድጋሚ የጊዜ-ሰሌዳ የሚያዝለት እና በማካካሻነት የሚሰጥ-ይሆናል።

ለሕክምና-ባልሆኑ ምክንያቶች - ሦስት (3) የትምህርት-አሰጣጥ ክፍለ-ጊዜዎች የሚያመልጧቸው ከሆነ፣ አገልግሎቶቹ ለጊዜው-እንዲቆሙ የሚደረግ እና መቅረቶቹ/absences - ፈቃድ ያላገኙ ይሆናሉ። ተማሪው-እንዳይሳተፍ ያደረገው እንቅፋት ምላሽ በሚያገኝ-ጊዜ፣ እና በተሰጠው የጊዜ-አቀማመጥ በቀደምትነት ለHHIP አገልግሎቶች በተያዘው የጊዜ-ሰሌዳ ውስጥ ተማሪ ለመሳተፍ ዝግጁ-ሲሆን፤ አገልግሎቶቹ ይቀጥላሉ። በአገልግሎቶቹ ላይ ጊዜያዊ-መቋረጥ መኖሩ፣ የHHIP አገልግሎቶችን የሚያራዝመው-አይደለም። አገልግሎቶች በሚያመልጥዋቸው-ጊዜ - በቀደምትነት ከተወሰነው የጊዜ-ሰሌዳ የተለየ የጊዜ-ሰሌዳ ለውጥን ሊያስከትል-ይችላል።

በአገልግሎቶች ላይ የሚደርሱ - ሁሉም መቅረቶች/absences፣ ስረዛዎች/cancellations፣ እና ጊዜያዊ-መቋረጦች/pauses፤ ወደ በትምህርት ቤት መሠረት ያደረገው የ'HHIP' ቡድን ሪፖርት-ይደረጋል።

## የደህንነት-ጥበቃ ቅድመ-ሁኔታዎች (Safety Precautions)

ከተማሪዎች ጋር የሚሰሩ - አገልግሎት-ሰጪዎች፤ ተገቢ-የሆኑ የግል መከላከያ መሣሪያዎች (personal protective equipment (PPE)ን - የ'KN95' ወይም ከዚህ-ጋር ተመጣጣኝ-የሆነ የፊት-መሸፈኛ ማስክ/mask - ቢያንስ መጠቀም አለባቸው። ቤተሰቦች፤ ተገቢ-ሆኖ ከተሰማቸው - አገልግሎት-ሰጪዎች ከተማሪው ጋር በሚሰሩበት ጊዜ፣ ጓንቲ፣ ጋውን፣ ቡት-ጫማዎች፣ ወይም ሌላ የ'PPE' መከላከያን እንዲያደርጉ ሊጠይቁ-ይችላሉ። የ'HHIP' ቢሮ፣ እነዚህን ነገሮች - ለአገልግሎት-ሰጪዎች ዝግጁ-ማድረግ ያለበት እና እነዚህ ዕቃዎች ከእያንዳንዱ-ጥቅም በኋላ መጣል-አለባቸው።

አገልግሎት-ሰጪው ወደ ተማሪው መኖሪያ-ቤት ወይም ወደ ሆስፒታል ክፍሉ ከመግባታቸው በፊት፣ ለተማሪው ኃላፊነት የወሰደው አዋቂ-ሰው ከበሩ-ላይ ሊያገኛቸው የሚያስፈልግ እና የሕመም መመልከቻ-ዝርዝር (Illness Checklist)[3] ላይ ምልከታ-ማድረግ አለባቸው። ይህ በመኖሪያ-ቤቱ ውስጥ ወይም በሆስፒታል ክፍሉ ውስጥ (የተማሪውን ሕመም ሳይጨምር) ማንም-የታመመ እንደሌለ ወይም ከታመመ-ሰው ወይም በCOVID-19 ቫይረሱ-እንዳለ የምርመራ-ውጤት ካለው ጋር የቅርብ ግንኙነት አለመኖሩን የሚያረጋግጥ-ነው።

እንደ DCPS ፖሊሲ[4] መሠረት፣ ተማሪው በCOVID-19 ቫይረሱ-እንዳለ የምርመራ-ውጤት በሚኖረው-ጊዜ፣ ለአምስት (5) ቀናት ተለይቶ-መቆየት አለበት። ክፍለጊዜዎቹ (Sessions) በዚህ ሰዓት - የሚሰረዙ ይሆናል። ከአምስተኛው ቀን በኋላ፣ ተማሪው ወይም በቤቱ-ውስጥ የሚኖር አባል ከምልክት-ነፃ የሆኑ ከሆኑ እና የ'HHIP' አገልግሎት-ሰጪው በመኖሪያ-ቤቱ ወይም በሆስፒታል ክፍሉ ውስጥ በሚሆን-ጊዜ ቫይረሱ እንዳለ (positive) የምርመራ-ውጤቱ ወይም ምልክቶቹ መታየት ከጀመረበት-ጊዜ በኋላ እስከ አስረኛው ቀን ድረስ፣ ማስክ (mask) የሚያደርጉ ከሆነ - ክፍለጊዜዎቹ (Sessions) ሊቀጥል-ይችላል።

የDCPS የሠራተኛ አባል፣ ለCOVID-19 ቫይረሱ-እንዳለ (positive) የምርመራ-ውጤት ካለው ወይም ህመም-ከተሰማቸው፤ በዚህ-ክፍል (section) ውስጥ ያለውን የደህንነት-ጥበቃ ቅድመ-ሁኔታዎች (safety precautions)ንም የሚከተሉ ይሆናል። በአገልግሎት-ሰጪው ሕመም ምክንያት የተሰረዙ ማንኛውም ክፍለጊዜዎች (sessions)፣ ዳግም-የጊዜ ሰሌዳ የሚወጣለት እና የሚካካስ-ይሆናል።

በቤት-ውስጥ የሚገኝ ማንም-ሰው ትኩሳት-ካላቸው (ማለትም፣ 100.4 ዲግሪ ወይም ከዚያ-በላይ የሆነ-ካላቸው)፤ የሆድ-ህመም - እንደ ማስመለስ ወይም ተቅማጥ፤ ወይም በመኖሪያ-ቤት ውስጥ እንዲቆዩ የሚያደርጋቸው-ሌላ ማንኛውም ሕመም ካለ፤ ክፍለ-ጊዜው ይሰረዛል። ሕመም የነበራቸው ሰዎች - ምንም-መድኃኒት ሳይወስዱ ለ48 ሰዓታት ከትኩሳት ወይም ከምልክት-ነፃ በሚሆኑ ጊዜ፤ ክፍለጊዜዎቹ/Sessions እንደገና-ይቀጥላሉ።

## የቤት-ስራዎች (Assignments)፣ የደረጃ-አሰጣጦች (Grades)፣ እና የክንውን-እድገት ሪፖርቶች

የ'HHIP' አገልግሎቶችን የሚያገኙ ተማሪዎች፣ በመደበኛው-ክፍሎች ውስጥ እኩዮቻቸው ልክ-እንደሚሰሩት አንድ-ዓይነት በሆነ መንገድ፣ እንዲያጠናቅቁ ይጠበቅባቸዋል። የአስተማሪ (ዎች) መዝገብ፣ ይህን ስራ ወደ 'HHIP' ቡድን ያቀርባሉ። ተማሪዎች፤ የ'HHIP' አገልግሎቶችን እያገኙ-ባሉበት ጊዜ፤ በክፍላቸው ውስጥ ላሉት ሁሉም አስፈላጊ-የሆኑ

መሣሪያዎች (material) ኃላፊነት-አለባቸው።

የ'HHIP' አገልግሎቶችን እያገኙ-ባሉበት ጊዜ፤ የትምህርት ቤት መዝገብ (The school of record)፣ የእድገት-ሂደት (Progress) ሪፖርቶችን እና ሪፖርት ካርዶችን ለተማሪው የማቅረብ ኃላፊነት አለበት።

---

[3] *Available at* Appendix A.

[4] *Available at* https://dcpsstrong.com/covid-19/.

## ጥያቄዎች እና ስጋቶች - አሏችሁ

የDCPS ‘HHIP’ ላይ - ሁሉም ጥያቄዎች እና ስጋቶች - ወደ ‘HHIP’ ቢሮ - በ202-939-3506 ወይም በhip.dcps@k12.dc.gov. መቅረብ-ይችላሉ።

## ይግባኝ-ማለት/አቤቱታ ማቅረብ (Appeals)

<u>የDCPS የ‘HHIP’ ቢሮ</u>

ተማሪዎች እና ወላጆች/አሳዳጊዎች፤ ውሳኔውን በተቀበሉበት በአስር (10) የቀን-መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ - የHHIP ቢሮን በማነጋገር፣ በ‘HHIP’ የብቁነት ውሳኔ ላይ - ይግባኝ-ማለት/አቤቱታ-ማቅረብ ይችላሉ። ይግባኝ-ማለት/አቤቱታዎችን ማቅረብ (Appeals)፣ የሚከተሉትን መያዝ አለበት:

- የተማሪ መረጃ፣ የሚከተሉትን-አካትቶ:
    - ስም፣
    - ትውልድ ቀን፣
    - የውስጥ መታወቂያ-(Local ID) ቁጥር፣
    - የትምህርት ቤት ስም፣ እና
    - ክፍል፣
- ይግባኝ-ለማለት ያስፈለገበት ምክንያት፣
- ይግባኝ-ለማለት/አቤቱታውን ለማቅረብ ያስፈለገበት ምክንያት - የሚደግፈውን የመረጃ-ስብስብ (Data) ወይም ሌላ ሰነድ፤ ሕክምናውን በሚያደርገው ሐኪም ተሞልቶ-የተጠናቀቀውን አዲስ የ‘HHIP Physician Verification’ ቅጽን አካትቶ-የያዘ። ይግባኝ-ለማለት/አቤቱታውን ለማቅረብ - የ‘HHIP Physician Verification’ ቅጽን ሞልቶ የሚያጠናቅቀው ሕክምናውን የሚያደርገው ሐኪም፣ ለመጀመሪያ መመራት (initial referral) ቅጹን ካጠናቀቀው ሐኪም ጋር አንድ-ዓይነት መሆን አለበት።
- ሐኪሙን ማግኘት-የሚቻልበት አድራሻ።

አቤቱታው - ወደ ‘HHIP’ ቢሮ በሚከተለው -መላክ አለበት:

- ኢሜል: hip.dcps@k12.dc.gov
- ፋክስ: 202-654-6020
- ደብዳቤ-መላኪያ/Mail:
  1200 First St.
  NE 8th Floor,
  Box 34
  Washington, DC 20002

ውሳኔው ከመደረጉ-በፊት፣ ሕክምናውን ካደረገው ሐኪም ጋር - DCPS መነጋገር አለበት። ሕክምናውን ካደረገው ሐኪም ጋር-ለመነጋገር መዘግየት የሚኖር ካልኖረ-በስተቀረ፣ በአምስት (5) ቀናቶች ውስጥ - አቤቱታው/The appeal እውቅና-ያገኛል።

<u>የዲሲ የስቴት የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (DC Office of State Superintendent of Education (OSSE)</u>

ተማሪዎች እና ወላጆች/አሳዳጊዎች፤ የOSSEን የመኖሪያ-ቤት እና የሆስፒታል ትምህርት አሰጣጥ አቤቱታ-ማቅረቢያ (Home and Hospital Instruction Appeal) ቅጽን[5] ሞልቶ-በማጠናቀቅ፣ የDCPS HHIP ብቁነት ውሳኔ ላይ - ለ‘OSSE’ አቤቱታ-ማቅረብ ይችላሉ።

አቤቱታውን በሚያስገቡበት-ጊዜ፣ አቤቱታውን-ያስገባው ሰው - መግባቱን-የሚያረጋግጥ የኢሜል ማረጋገጫ የሚላክለት እና፣ የ‘OSSE’ ሠራተኛ-የሆነ ሰው፣ በአቤቱታው እና በሽምግልናው ላይ የሚቀጥለው እርምጃዎች ምን-እንደሚሆኑ ለማሳወቅ ያነጋግራቸዋል።

[5] *በሚከተለው ላይ መገኘት የሚችል፣* https://forms.office.com/pages/responsepage.aspx?id=8Unkj5SLt0-ZBm-Tnagtc4fbigKQO8FIiff7 C0X0atxUOFNDMVpHVzk3TkxONVUzMU9LVjVMUlpNVi4u.

## አባሪ (Appendix) A

# የመኖሪያ ቤት እና የሆስፒታል የትምህርት-አሰጣጥ ፕሮግራም (Home and Hospital Instruction Program) የሕመም መመልከቻ-ዝርዝር (Illness Checklist)

**ትዕዛዛት (Directions):** የ'HHIP' ቡድን አባላቶች፣ ወደ ተማሪዎች መኖሪያ-ቤቶች ከመግባታቸው አስቀድሞ፣ የሚከተለውን የመመልከቻ-ዝርዝር (checklist) - ይመለከታሉ። ከእነዚህ ማንኛውም አንዱ ነገር መልሱ "አዎን/yes" ከሆነ፣ ክፍለ-ጊዜው/session - ወዲያውኑ ይሰረዛል። በመኖሪያ-ቤቱ ውስጥ ያሉት - ምንም-መድኃኒት ሳይወስዱ ለ48 ሰዓታት ከምልክት-ነፃ በሚሆኑ ጊዜ፤ ክፍለጊዜዎቹ/Sessions እንደገና-ይቀጥላሉ። በመኖሪያ-ቤት ውስጥ ያለ-ማንኛውም ሰው - የCOVID-19 - ቫይረሱ-እንዳለበት (positive) መሆኑ በምርምራ-ከተረጋገጠ፤ የ'HHIP' አገልግሎት-ሰጪው በመኖሪያ-ቤቱ ውስጥ በሚገኝ ጊዜ፣ ቫይረሱ-እንዳለበት (positive) መሆኑ በምርምራ-የተረጋገጠው ሰው፣ የፊት-መሸፈኛ ማስክ (mask) ማድረግ የሚችል ከሆነ - ከአምስት (5) ቀናት በኋላ ክፍለጊዜዎቹ/Sessions እንደገና-ይቀጥላሉ።

**ጥያቄ:** ባለፉት 48 ሰዓታት-ውስጥ፣ ተማሪው ወይም በቤታችሁ-ውስጥ የሚኖር ሰው፣ ከሚከተሉት ምልክቶች ውስጥ ማንኛውንም-ዓይነት ነበራቸው:

☐ ሣል ወይም የመተፋፈን-ስሜት፣ ንፍጥ-መብዛት፣ ማስነጠስ

☐ ትኩሳት (100.4° F ወይም ከዚያ-በላይ የሆነ)

☐ ብርድ-ብርድ ማለት

☐ እራስ-ምታት፣ የሰውነት-ህመም፣ የጉሮሮ ቁስለት ህመም

☐ ድንገተኛ የሆነ ጣዕምን ወይም ሽታን-ማሽተት ማጣት/መጥፋት

☐ ማቅለሽለሽ፣ ተቅማጥ፣ ማስመለስ፣ ወይም የመፍዘዝ-ስሜት መሰማት

☐ ከመጠን-ያለፈ፣ ሊገለጽ-የማይችል ድካም፣ ወይም በድካም-መዛል

☐ የትንፋሽ ማጠር ወይም ለመተንፈስ መቸገር (በአስም-ወይም በአለርጂ ምክንያት ያልተፈጠረ)

☐ አዲስ፣ አመጣጡ-ሊገለጽ ያልቻለ ሽፍታ፣ እብጠቶች፣ ቁስለቶች፣ ወይም ከመጠን-ያለፈ የቆዳ ማሳከክ

☐ ከጤና-እንክብካቤ ሰጪው እንደበሽታ-ሆኖ የታወቀ፣ አዲስ ወይም ተላላፊ-የሆነ በሽታ

☐ የ'COVID-19' ወይም ሌላ ተላላፊ-በሽታ - በሽታ-እንዳለበት ከታወቀ (positive) ሰው ጋር፣ የቅርብ-ግንኙነት ነበረው ተብሎ-የተመነበት፣ (የሚከተሉትን-አካትቶ፣ ነገር-ግን በእነዚህ ብቻ ሣይወሰን፤ ጉንፋን፣ የጉሮሮ-ሕመም፣ 'hand-foot-mouth'፣ ኩፍኝ/chicken pox፣ ወዘተ...)